# ፕሮፌሰር ሐይሌ ላሬቦ አስቀየሙን (ሰመረ አለሙ)

semere.alemu@yahoo.com

ባለፈዉ የተከበረዉ የኢትዮጵያ ልጅና የአንድነት ሀይል ፕሮፌሰር ሐይሌ ላሬቦ ባልተለመደ መልኩ በኢሳት መስኮት ቀርቦ ኢትዮጵያዊነትን አስመልክቶ በምሁር እይታዉና በሀገር ወዳድ ምልከታዉ ለሁሉም በማያዳላ መልኩ ታሪክንና ኢትዮጵያዊነትን እንዳለ በመልክ በመልኩ አስረድቶን ለማመሰገን ቃላት ስንመርጥ በተከታዩ ቀን ከሌላዉ የኢሳት ማእከል ሌላዉ ጋዜጠኛ ኢትዮጵያዉያንን ይቅርታ እንጠይቀለን ሐይሌ ላሬቦ ኢትዮጵያዉያንን አስቀይሞብናል የሚል ዜና ሰማን። የዚህ ነገር ዉዥንብር እስኪጣራ ግራ ተጋብተን እያለ ሐይሌ ላሬቦ እንደገና በግሉ ማብራሪያ ሰጠበት እኛም የነገሩን ጭብጥና አቡዋራዉን ያስጤሰዉን ነገር አገኘነዉ። ተከፉ የተባሉ ወንድሞቻችን ያስቀየማቸዉ የኦሮሞ ህዝብ እረኛ ነበር የሚለዉ አጠራርና ባጠቃላይ ለነገዱ የተሰጠዉ መጠሪያ መሆኑ ተገለጸልን።

መጀመሪያ በፈረንጆቹ ቀጥሎ የትላንት ጠቅላይ ግዛታችን ኤርትራና የህወአት አስተዳደር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በርትተዉ በመሰራታቸዉ እኛም በማንቀላፋታችን ዛሬ እነዚህ ወገኖች ላይ ሀሳቡ ፍሬ አፍርቶ ልባቸዉ ባገራቸዉና በወገናቸዉ እንዲሁም በታሪካቸዉ ላይ እንዲሸፍቱ ሁኗል። በእርግጥ ሐይሌ ላሬቦ እነዚህን ወገኖች የተናገረዉ አስቆጥታቸዉም አይመስልም ምክንያቱም ባለፈዉ ፕሮፌሰር ህዝቅኤል ከዚህ በባሰ መልኩ ነገር አሳመርኩ ብሎ አጥግቦ ሰድቧቸዋል ካማኝ የነገረኝ የሚባል ብሂል አለ።

ሐይሌ ላሬቦ በዚያ መግለጫዉ ጋዜጠኛዉ ለጠየቀዉ መልስ የኢትዮጵያን አመሰራረትና በየጊዜዉ የሚነሳዉን ተረት ተረት አጥርቶ ማለፍ ስላለበት ከሙያዉ አንጻር በማያሻማ መልኩ በዚህ ነገር እንዳንመላለስ ማህተም አትሞበት አልፏል በዚህም ሊመሰገን ይገባዋል ካንድ ምሁር የሚጠበቀዉም ይኸዉ ነዉ። በዚያ ቃለ ምልልስ ሐይሌ ላሬቦ ባብዛኛዉ የኦሮሞን ህዝብ ታላቅነትና በኢትዮጵያ ግንባታ ያደረገዉን አስተዋጽኦ ነበር የዘከረዉ ነገር ግን የሐይሌ ላሬቦ ከሳሾች ወደሁዋላ ተጉዘዉ ታሪክ አጣቅሰዉ ማህደር አስደግፈዉ የተናገሩበት አንድም የአለም መድረክ አላየንም ይልቁንስ የአንድነት ሐይሎች ከነሱ ልቀዉ የኦሮሞን ህዝብ የሚያኮራ ደጎስ ያለ ድርሳናት አስነብበዉናል።

ማንም ሆነ ማንም ፈረንጆች ከነገሩዋቸዉ አስተሳሰብ ዉጭ ከተሄደ በኦሮሞ ጠላትነት ይፈረጃል ቀጥሎ ዘመናዊ ገዳ ይካሄድበታል እንዲህ አይነት አሸባሪ ድርጊቶች በፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ፤ በፕሮፌሰር ጌታቸዉ ሐይሌ፤በዶክተር ታየ ወ/ሰማአት፤በአቶ አሰፋ ጫቦ፤ በኢንጂነር ሐይሉ ሻዉል፤በቴዲ አፍሮ፤ በአቶ ግርማ ካሳ፤ደምስ በለጠ፤ በሔኖክ የሺጥላና በሌሎችም በተለያየ መልኩ ተካሂዷል። በበኩሌ ሐይሌ ላሬቦ መሀመድ ግራኝን አስመልክቶ የተናገረዉ አልተመቸኝም ስፍር ቁጥር የሌለዉን ቤተ ክርስቲያናት ያቃጠለ ዜጋ የፈጀ በሀይሌ ላሬቦ ምልከታ ሌላ ቦታ ይዟል እኔን ያልተመቸኝን በመናገሩ ከኑሮዉ እንዲሰናከል ክብሩም እንዲነካ አልፈቅድም እኔም በተለያዩ ጉዳዮች የራሴ ምልከታ ስላለኝ የሱንም አከብራለሁ ከእኔ ምልከታ አንጻር ግን ትክክል ያለመሆኑን አስረዳለሁ በዚህ ሁኔታ የሚዳኙን ሌሎች ይሆናሉ ማለት ነዉ እነሱም የራሳቸዉ የመመሪያ ስልት ይኖራቸዋል እዉነትን የሚያጣሩበት።

በወቅቱ በህብረተሰብ እድገት ዛሬም ቢሆን የኦሮሞ ነገድ ከከብት ጋር ቁርኝት ያለዉ ነዉ ከብቶችም የሀብት ምልክት ናቸዉ ዛሬም ድረስ። ከብቶች ሲዋለዱ ሰፊ ቦታ ያስፈልጋቸዋል ያንን ለማስከበር የኦሮሞ ነገድ አካባቢዉን እያሰፋ ሄደ ይህ ሂደት ደግሞ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ይጨምራል በስምምነት ቦታህን ልቀቅ

ስለማይባል ይህን ተከትሎም ሰፌ እልቂት ይሆናል ። እንግዲህ በከብት እርባታ(ፓስቶራሊዝም) የተሰማራ ህብረተሰብ እረኛ ነበር ማለቱ ስህተቱ ምንደነዉ እስከዛሬስ ይህን የሚተካ ምን ቃላት አሉን? ወይስ በወቅቱ የኦሮሞ ነገድ በከብት እርባታ ሳይሆን በሀይ ቴክ (high tech) ላይ የተሰማራ ነበር እንበል? ትልቅ የሚያደርገዉን ነገር የኦሮሞ እንባ ጠባቂ ነን የሚሉት ያሳንሱታል። ታላላቅ ጀግኖቻቸዉን ከኢትዮጵያ ጋር በማቆራኘት ስማቸዉን ጥላሸት ይቀባሉ። ነብሱን ይማረዉና ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን ኦሮሞ ነዉ በኦሮሞነቱም የሚኮራ ነዉ ምንም እንኳን አዲሶቹ ኦሮሞ ነን ባዮች ወይም ደግሞ የታብሎይዱ ተስፋዬ ገ/አብ ገዳ ቢጠሉትም። በጥልቅ እዉቀቱ ወደር የማይገኝለት ሎሬት ጸጋዬ በአንድ ጽሁፉ ጋላ የሚለዉን መጠሪያ "የጸሀይ ብርሀን ፋና" ነዉ ብሎት ያለፈዉ።

እንግዲህ ሎሬት ጸጋዬ ከተስፋዬ ገ/አብ ገዳ፤ ከሁለቱ ሌንጮዎች፤ ከህዝቅኤል ጋቢሳ፤ ከጸጋዬ አራርሳ ያነሰ ኦሮሞ አልመሰለኝም። በእርግጥ ከሎሬት ጸጋዬ በላይ ፈረንጂ የነገረንን እናምናለን ብለዉ ከተቀበሉ ምርጫቸዉ የነሱ ነዉ በዚህ ቅዋሜ በበኩሌ የለኝም ታሪክን ወደሗላ ሂዳችሁ አታመሳክሩ ማለት ግን እዉቀት ላይ የተፈጸመ ወንጀል በመሆኑ አቅሙ ያለዉ ምሁር ሊቋቋመዉ ይገባል። አለሙን የሞላዉ የኦሮሞ ምሁር እያለ የኦሮሞን ታሪክ የሚጽፉት አስመሮም ለገሰና ተስፋዬ ገ/አብ ናቸዉ በእርግጥ እነዚህ ግለሰቦችና ሻቢያ ለኦሮሞ ስስ ልብ ነሯቸዉ ነዉ ወይስ ደካማ አእምሮ ፈልገን ዘራችንን እንዝራ ብለዉ በማሰባቸዉ ነዉ? መልሱን ለጊዜ እተወዋለሁ። ቀደም ባለዉ ጊዜ ከላይ በጠቀስኳቸዉ ወገኖች ላይ አድማና ስም ማጥፋት ተካሂዷል በእርግጥ አብዛኛዉ የሳይበር ጥቃት ቢሆንም በሐይሌ ላሬቦና በቴዲ አፍሮ ላይ ግን መተዳደሪያ ላይ ያነጣጠረ ከፉ ዘመቻ ነበር። በወቅቱ የአንድነት ሐይሉ በቂ ምላሺ ባለመስጠቱ በክፉ ስራቸዉ ተበረታተዉ ዛሬ ሐይሌ ላሬቦ ላይ በድጋሚ ተመሳሳይ ዘመቻ ከፍተዉበታል።

ሐይሌ ላሬቦ ሌሎችም ከላይ የጠቀስኳቸዉ ግለሰቦች በወቅቱ እንዲህ ያለ ዘመቻ የተዘመተባቸዉ በግል ጉዳያቸዉ ሳይሆን ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ለማድረግ ጥረት በማድረጋቸዉና የዜግነት ግዴታቸዉን በመወጣታቸዉ ነዉ።የሚያሳዝነዉ በወቅቱ የአንድነት ሐይሉ የተወረዉን ድንጋይ መልሶ ባለመወርወሩ እነዚህ ወገኖች ዱላዉን ብቻቸዉን ተቀብለዉታል። እንደዉም አንዳንድ የሚዲያ ተቋማት የጸረ ኢትዮጵያ ሐይሎች መጠቀሚያ ሁነዉ የገዛ ወገናቸዉን አስደብደበዋል ለዚህም ኢሳት በዋናነት ይጠቀሳል G7 የተባለዉም ድርጅት እንዲሁ ከበሬታና አንድነቱን ከነዚህ ገንጣዮች ጋር አስተካክሏል። ሌሎቹ በዚህ ነገር አቅዋም እንዲወስዱ ቢጠየቁም ግርግሩን ለድር ገጻቸዉ አድማቂነት በመፈለግ የዜግነት ግዴታቸዉን ሳይወጡ ቀርተዉ አገር ለማበጣበጥ አንድነትን ለማላላት የግል አስተዋጽኦ አድረገዋል።

ሌላዉን ወደ ጎን ትተን የኢትዮ ሚዲያዉ አብረሀ በላይ የሻቢያዉን ተስፋዬ ገ/አብ ጽሁፍ አላስተናግድም ብሎ እስከ አሁን ባቋሙ ጸንቷል በዚህ ነገር ብቻ ልናመስግን እንወዳለን። በመስታወት ዉስጥ ያለ ሰዉ ድንጋይን ለመወርወር የመጀመሪያዉ አይሆንም።ጁዋር መሀመድ በሀጂ ነጂብ አማካይነት የዝግ ስብሰባ ተደርጎ ፕላኑን ሲናገር ክርስቲያን ያልሆነዉን ሁሉ በሜንጫ መቅላት ነዉ ብሎ ለተከታዩ ሲናገር ተከታዩ በታላቅ ጭብጨባ ሃሳቡን ሲያጸድቅ ሐጂ ናጅብ እንዳነተ አይነቱን ያብዛልን ያሉት ቪዲዮ በእጃችን ይገኛል ይህን ተከትሎም ክርስቲያኑ እና አብያት ክርስቲያናት ላይ ከፍተኛ ጥቃት ደርሷል ንብረት ወድሟል ዜጋ ተገድሏል። (https://www.youtube.com/watch?v=RMLLmAMWdG8) ጁዋር መሀመድ ብልግናዉን ከጨመረበት ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ንቆ አረባዊነትን ከመረጠ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ ከችሎታዉ

በላይ ከተለጠጠ፤ ምድር ላይ ካለዉ እዉነታ ይልቅ ጭብጨባና ተረትን ከመረጠ፤ የአንድነት ሐይሎችን ሆነ ብሎ መተናኮሎን ካላቆመ የአንድነት ሐይሎች በየጊዜዉ ያደረገዉን የድንፋታ ንግግር እና የሜንጫዉን ጨምረን ይህን እንቅስቃሴ ወደሚጠሉ ተቋሞች እንደምንሄድ ሊያዉቀዉ ይገባል https://www.youtube.com/watch?v=1ulCobhc3DM። ተስፋዬ ገ/አብ ገዳም ከዚህ የተለየ እድል አይኖረዉም አኖሌን አስከትሎ ለደረሰዉ እልቂት ። ሌሎች ሐይሌ ላሬቦ ላይ ያነጣጠሩት የአለፍ አመራርና አቀንቃኞች የነበሩ በአርባ ጉጉ፤ በበደኖ፤ በሀረር እና በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ዘርን በማጥፋት በቀጥታ የተሳተፉ በመሆናቸዉ የነሱም መረጃ በእጃችን ስለሚገኝ እነሱም በህግ ፊት ስራቸዉ ወደ ሗላ ተኪዶ ይመዘናል። ባለፈዉ አቶ አሰፋ ጫቦ በህይወት እያለሁ ታሪክ እንዲህ መላ ቅጡን ሲያጣ አላይም በማለት ሰዉ የተቀጠፈበት፤ ወገን ባሪያ ተብሎ የተፈነገለት በኦሮሞዉ አባጅፋር በመሆኑ በዛ ለተፈነገሉት ወገኖቻችን ላይ ጂሬን የተባለ ቦታ ከአኖሌ የገዘፈ ሐዉልት ይሰራልን በማለት በተረት በጥላቻ ሳይሆን ታሪክን አስጨብጦ ማህደር አያይዞ አቅርቦልናል።ታዲያ አሰፋ ጫቦ እንደ ሌሎቹ ሲተፋበት ስለማይቀበል ከገፋም ለህግ ስለሚያደርሰዉ ሀሳቡ በጉምጉምታ እና በፓል አልሞ ተኳሾች ሙከራ ተደርጎ ነገሩ በአቶ አሰፋ ጫቦ ቁጥጥር ስር ዉሏል። ሰዉየዉ ክፉ ነዉ ተደብቀዉ ሊያጠቁት ቢየስቡም ሊደርስበት ይችላል መጠንቀቅ ጥሩ ነዉ። ቀደም ባለዉ ጊዜ በላከሁት መልእክት የኢሳት ዋና አላማ በድፍረት ሊፈተሺ ይገባል። የኢትዮጵያ ባንዲራ ተሸፍኖ የአለፍን ባንዲራ ያቀረበልን፤ ለኢሳይያስ አፈወርቅና ለመንግስቱ አፈቀላጤ የሆነ የሚዲያ ተቋም ዛሬ ሐይሌ ላሬቦ ታሪክን ታሪክ በማድረጉ ይቅርታ እንዲጠየቅ ያስገደደዉ ሐይል ማን እንደሆነ የኢሳት ተከታታዮች ሊያጣሩ ይገባል እላለሁ።

እዚህ ላይ አያቆምም ጁዋር መሀመድ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ብሎ በአለም አቀፍ የሚዲያ ተቋም የመሰከረዉን ስቱዲዮ ድረስ ጋብዞ ለዳግማዊ ስድብ ማመቻቸት አላማዉ ምንድነዉ? ከጁዋር ባላነሰ የቀድሞ አለፍ አባላት እና የኦሮሞ አክትቪስቶችስ ነን የሚሉት አላማቸዉና አካሄዳቸዉ እየታወቀ የኢሳት እሽሩሩ ከምን የመጣ ነዉ? የራሳቸዉ የሆነ ከበቂ በላይ ሚዲያ ይዘዋል ለመግባቢያነትንም ቁቤን መርጠዋል ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ጋብዞ የአንድነት ሐይሉ እንዲላላ፤ እንዲሳከር፤እንዲወናበድ ማድረግ ጠቀሜታዉ ለማን ነዉ? ባጠቃላይ ኢሳት በኢትዮጵያዉያን መዋጮ የሚንቀሳቀስ ድርጂት ይመስለኛል በእርግጥ ስርጭቱና ሽፋኑን የሚሰጣቸዉ ፕሮግራሞች እንደ ተዋጣዉ ገንዘብ ከሆነ ሻቢያና የአረብ አገሮች ይደግፉታል የሚባል ጭምጭምታ ስላለ ኢሳት የህዝብ ወይም public organization በመሆኑ አመታዊ ሒሳቡን በድረ ገጹ በግልጽ ለሚፈልገዉ ለእይታ ማብቃት ግዴታዉ ይመስለኛል የሀገሩም ህግ ያዛል። ይህም ማለት ገንዘቡ ከየት እንደመጣና ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚዉል በዝርዝር እንዲቀርብ ሕጉ ያስገድዳል ።

ይህ የሚዲያ ተቋም ጁዋር መሀመድ፤ ዳዉድ ኢብሳ፤ በያን አሶባን በአክብሮት ጋብዞ ተክሌ የሻዉን፤ ሐይሌ ላሬቦን፤ አሰፋ ነጋሺን ማበሻቀጡ የጤንነት ስላልሆነ እኛም አማራጫችንን እናጠንክራለን ጂብ ካለፈ ዉሻ ጮኸ እንዳይሆንብን። ለማጠቃለያ ኢትዮጵያዉያን በአንድ ሳምባ እንደሚተነፍስ ሁሉ እንደ መንጋ አንነዳም የማስተዋል የረቀቀ አእምሮ አለን እንዲህ አይነቱን ምልልስ የምናደርገዉ ነገርን ለማጥራት እና አንድነታችንን ለማጠናከር አንጂ ወያኔ እንደሚያስበዉ ለመበላላት አይደለም ጽሁፉ ያነጣጠረዉ ኦሮሞን ወክለናል ለሚሉ ዉክልና ለሌላቸዉ በአላማ ከወያኔ ላልተለዩ ለአንድነት ጠላቶች መሆኑ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ።እዚህ ላይ የኦሮሞ ህዝብ በታሪክ የተከበረ ቦታዉን ይይዛል ኢትጵያዊነትንም ያጠነክራል።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር**